# ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

**ዴሞክራሲያ ቅጽ** 37 **ቁጥር** 4 **ሚያዚያ** 2004 **ዓ.ም**

## <u>የአርባ ዓመት የትግል ፅናትና የሀገራችን ኢትዮጵያ ሁኔታ</u>

## ከ1964 ሚያዝያ - እስከ ሚያዚያ 2004

## <u>ልዩ ዕትም</u>

በሀገራችን ኢትዮጵያ በሦስቱም ሃይማኖቶች ምዕመናን በኩል፣ አርባ ዓመት የዘመን ስሌትና ቀመር፣ የተለየ የታሪክ ሂደትና ዕልባት እንዳለው ይነገራል:: በያንዳንዱ አርባ ዓመት ሁኔታዎችና ክስተቶች ሲፈራረቁ፣ ለደግም ይሁን ለክፉ፣ አንድ የታሪክ ክስተት ይመዘገባል ተብሎም ይነገራል:: ለዚህም የዕምነት አባባል ማጠየቂያ የሚደረገው፣ ከአራት መቶ ዓመታት ከፈርዖን የባርነት አገዛዝ በኋላ፣ ነፃነታቸውን ለማግኘት የተሰደዱት ዜጎች የተመኙትን የነፃነት ሀገር (ምድረ-ከናዓን) ለማግኘት ሲጓዙ አርባ ዓመታት እንደፈጀባቸው የሚጠቀስ መሆኑን ነው:: በእኛም ሀገር ይህንን አባባል ለማስረገጥ የአርባ ዓመትን የጊዜ ቀመር ፣ ከዕምነት ጋር ለማያያዝ የሚደረግ ጥረት አልፎ አልፎ ይሰማል::

በአስራ ስምንት መቶ ሰማንያ ስምንት (1888) ዓመተ ምህረት በአድዋ ጦርነት ድል የተመታችበትን የሀፍረት ሽንፈት ለመበቀል ኢጣሊያ አርባ ዓመት እንደፈጀባትና የማይጨውን የአስራ ዘጠኝ መቶ ሃያ ስምንቱን (1928) ወረራ ለመፈፀም የአርባ ዓመት መሰናዶ እንዳደረገች፣ ኢትዮጵያውያን አዛውንት ያገናዝባሉ:: ከአምስት ዓመታት የአርበኝነት ትግል በኋላም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትንና መልካም አስተዳደርን ለማግኘት ወደ አርባ ዓመታት (1933-1966) የሚጠጋ (በየጊዜው አመጾች ቢኖሩም) ትዕግስት በማድረግ፣ የየካቲት 66 ዓም ሕዝባዊ አመፅ አካሂዶ የሥርዓት ለውጥ ለማየት በቅቶ ነበር::

የኢትዮጵያ ሕዝብ የመከራ ፅዋው ሞልቶ እስኪገነፍል ድረስ፣ እንደገና ሌላ አርባ ዓመታት የፈጀ ትዕግስት ማድረግ ይኖርበታል የሚል ምፀትና መርገምት ከሌለ በስተቀር፣ የአስራ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ስድት (1966) ዓም የካቲት ሕዝባዊ አመፅ ከገነፈለ ይኸው አርባ ዓመት ሊሞላው ምንም ያህል አልቀረ:: ያለፉት ዓርባ ዓመታት ከአንድ መከራ ወደ ሌላ አዳዲስ መከራ፣ የተንከባለለበት ዘመን ከመሆን ያለፈ ያመረቃ ተስፋና የብርሃን ጭላንጭል የታየበት ወቅት አይደለም:: እርግጥ ለውጥ ታይቷል ከተባለ፣ ለአምባገነን ገዥዎችና ለዘረኞች ደስታና ተድላ፣ ሠርግና ምላሽ ከመሆን አልዘለለም:: የዋርካ ዛፍ ፍሬ ማፍራት ለአዕዋፋት እንጅ ለዋርካው ዛፍ እንዳልጠቀመው

ሁሉ ፣ በኢትዮጵያ የለውጥ መምጣት የጠቀመው ቢኖር፣ የገዥውን ክፍል ብቻ እንደሆነ ያለፉት አርባ ዓመታት ኩነቶች በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጠውታል።

ባለፉት አርባ ዓመታት የተሰውት የኢትዮጵያ ሰማዕታት፣ አሁን ያለችውን ኢትዮጵያን የማየት ዕድል ቢገጥማቸው ኖሮ ፣ ከማዘንና ከመገረም የተነሳ ፣ ክቡር አፅማቸው ከመካነ መቃብሩ ውስጥ ሆኖ ከመገለባበጥ አይቆጠብም ነበር። ምክንያቱም፣ ታላቅና ጥንታዊ የሆነችው ሀገራቸው፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት ሰፍኖባት ፣ ዜጎቿ በእኩልነትና በብልፅግና በሰላምና በዕድገት ጎዳና መጓዝ አለባቸው ሲሉ የታገሉበትና ለዚህም ሲባል የመጨረሻውን መስዋዕት የከፈሉላት ኢትዮጵያ፣ ዛሬ በብሔረሰብና በሃይማኖትም ሳይቀር ተከፋፍላ በዘረኞች አምባገነን አገዛዝ ስር ወድቃ በማግኘተታቸው ነው። የአርባ ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ መሥዋዕት ያስከፈለ ትግል ውጤት ፣ ሀገሪቱ አሁን ካለችበት አሳዛኝና አሰቃቂ ሁኔታ መድረሱን የሚያይ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ፣ ከመኖር ይልቅ መሞቱን መርጦ ተቀምጧል። በባርነት ተዋርዶ ከመኖር ይልቅ ፣ በነፃነት ተከብሮ መሞትን የታሪኩ ምርጫ ያደረገ ዜጋ ሁሉ፣ በዘረኞች ጫማ እየተረገጡ ከመኖር ይልቅ፣ ክተት-መክት ብሎ ከመነሳት የተለየ ሌላ ምርጫ ሊኖረው ከቶ ስለማይችል ነው። ይህ ምርጫ ደግሞ፣ ይዋልም ይደር እንጅ ሕዝባዊ ውሳኔ የሚያገኝበት ወቅት እንደሚመጣ ማንም ሊጠራጠር አይችልም።

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፣ ከአርባ ዓመታት የሽብር፣ የስቃይ፣ የእስራት፣ የግድያ፣ የስደት፣ የውርደት፣ የሀፍረትና የጥቃት ዘመን በኋላ፣ ከነጭራሹ የኅልውናዋ ጉዳይ በከፍተኛ ደረጃ አስደንጋጭ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይህንን አስደንጋጭ ሁኔታ እንዳልባሌ ጉዳይ ሊቆጥሩትና ሊያቃልሉት የሚፈልጉት፤ ወያኔዎችና ተባባሪዎቹ ፣ እንደዚሁም የኢትዮጵያን ጥፋት የሚመኙ ታሪካዊ ባዕዳን ጠላቶች ብቻ ናቸው። ለዚህም በቂ ምክንያት አላቸው። ምክንያቱም፣ ባዕዳን ጠላቶች፣ ጥንታዊትና ታሪካዊት ኢትዮጵያ እንደ አንድ ሀገር፣ ዜጎቿም እንደ አንድ ሕዝብ መቀጠል የለባቸውም ብለው ስለወሰኑ ነው። ይህንን የቆየ ኅልማቸውን ዕውን ለማድረግ ደግሞ ፣ ወያኔ የሚባለውን ከሃዲ ቡድን እንደ "ትሮጃን" ፈረስ ይጠቀሙበታል። ወያኔ የራሱን ሰብዕና የሸጠ ብቻ ሳይሆን ፣ ሀገሩንና ታሪኩን ሕዝቡንም ጭምር የካደና ያዋረደ በመሆኑ ፣ የባዕድ አገልጋይ መሆን ወይም አለመሆን በኅሊናው ውስጥ የሚብሰለሰል ጉዳይ አይደለም። የኅሊና ጉዳይ ከተወሳ ደግሞ ፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የኅሊና ክብርም ይሁን ዋጋ ፣ ፍርድም ይሁን ግንዛቤ ጋር የሚፃረር አመለካከትና ድርጊት ወያኔ ሲፈፅም ባልተገኘም ነበር። ክኅደትን እንደፀጋ ፣ ውርደትን እንደ ክብር፣ ውሸትን እንደ ዕውነት፣ ዘረፋን እንደ ብልጠት፣ ግድያን እንደ ጀግንነት፣ ቂም በቀልን እንደ ግል ደስታና የመንፈስ ዕርካታ፣ ይሉኝታን እንደ ቂልነት ፣ ማጭበርበርን እንደ ዕውቀት የሚቆጥር ቡድን ፣ በኢትዮጵያ ምድር የተፈጠረ መሆኑ እስከ አሁን ድረስ እየተገረሙ ያሉ ዜጎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ከተመሠረተ ይኸው አርባ ዓመቱን (ሚያዝያ 1964-- ሚያዝያ 2004 ) አስቆጠረ ፤ አከበረ። ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባውን ብሔራዊ ቃል-

ኪዳን እያከበረ ትግሉን ቀጠለ። ድፍን አርባ ዓመት! በነኝህ አርባ ዓመታት የትግል ታሪኩ፣ ዕልፍ-አዕላፍ የኢትዮጵያ ጀግና ልጆችን አፍርቷል ። በአዕላፍ የሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች ብርቅ ሰማዕታቱንም አጥቷል። እነኝህ ሰማዕታት የፈለቁት፣ የተሰባሰቡበት የተደራጁትና ወደ ትግል ጎራ የተሰማሩት በኢትዮጵያዊነታቸው፣ ለኢትዮጵያና ለሕዝባቸው የገቡትን ሀገራዊ ተልዕኮ ለመፈፀም ነው። ሁላቸውም የፈለቁት፣ የወጡት ፣ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክና ማኅፀን ነው። የመነሻ መድረሻቸው ዒላማ ያነጣጠረው ፣ በኢትዮጵያ ጥቅምና ብሔራዊ ልዕልና ፣ በዜጎቿ እኩልነትና ነፃነት ላይ ነው። የትግል አድማሳቸው ፣ ከኤርትራ አፋፍ እስከ ኤሉባቡር ጫፍ፣ ከፈርፈር እስከ ሁመራ፣ ከጋምቤላ እስከ ኦሜድላ ነበር። ራዕያቸው ብሔራዊ፣ ፍቅራቸው ሕዝባዊ፣ ወገንተኝነታቸው ሀገራዊ፣ አመለካከታቸው ካድማስ ባሻገር ፣ መስዋዕታቸው ከዳር እስከ ድምበር ነበረ። ለኢሕአፓ ታጋዮች ፣ የሀገርና የሕዝብ ፍቅር የሚገለፀው ፣ በወረቀት ላይ ሰፍሮ በሚታይ የሰላማዊ ሰልፍ መፈክር ሳይሆን ፣ የደምና አፅም መሰዋዕት በመክፈል ነው። ከጥንት ጀምሮ ፣ ለኢትዮጵያ ራሳቸውን መሥዋዕት የሚያደርጉት ደግሞ ፣ የአገርና የወገን ፍቅር ያንገበገባቸው ናቸው። ይህን የታሪክ ጋሻ ያነገቡና ህይዎታቸውን የሚከፍሉ ሁሉ፣ የታደሉና የተከበሩ ናቸው። የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች የሚባሉትም፣ ለከንቱ ውዳሴ አይደለም!
ለዚህም እኮ ነው ጓዶቻችን፡-

"እንደ ፍልስጤም ደም፣ በሲናይ በረሀ ሁሌ እንደሚፈሰው፣
የእኛውም ደም ፈሶ አፈሩን አርጥቦ መሬቱን ያራሰው፣
የመከራው ደወል ደም የተበከለ፣ ድምፅ ለማሰማት እየተደወለ ፣
መረዋው ዝም አይልም ዓላማውን መትቶ ካልተገላገለ!"

እያሉ የጀግና ጎልፈት ያለፉት። ትግሉን የቀጠለውም ኃይል የሚራመደው ይህንን የማይናወጥ መርኅ በመከተል ነው ።

ፓርቲው ባይበገሬነት ትግሉን ሊቀጥል የቻለውም አብነቱና መሠረቱ፣ ይህ በመሆኑ ነው። የትግል ታሪኩ አልፋ-ዖሜጋ፣ እኩልነትና ደሞክራሲያዊነትን የተላበሰ ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነው። የዓላማና የራዕዩ መነሻና መድረሻም የተሸበበው፣ በኢትዮጵያዊ ሃብል ሲሆን፣ የዜግነቱ እትብት፣ ባኅርዩና ምግባሩ፣ የጎልውናው ውስጠ-ምሥጢሩ፣ የሰብዕናው ሁለንተናዊ መግለጫው፣ ይኸው በመሆኑ፣ የአርባ ዓመታት የትግል ውጣ-ውረድን ተቋቁሞ እዚህ የደረሰው በፅኑ ኢትዮጵያዊ መሠረት ላይ የተቋቋመ ድርጅት በመሆኑ ነው። "ለአለፉት አርባ ዓመታት፣ በየወራቱ እንደእንጉዳይ እየፈላ የከሰመው ድርጅትና ስብስብ ፣ እንደ ጉም ሽንት ተበትኖ ሲጠፋ ፣ ለምን ኢሕአፓ እስካሁን በፅናት ቆየ?" የሚለውን ጥያቄ የሚጠይቅ ዜጋ ካለ፣ መልሱን ከኢሕአፓ ኢትዮጵያዊነት ማኅድር ውስጥ እንደሚያገኝ በዕርግጠኝነትና በኩራት መናገር ይቻላል።

በዕርግጥም ምንጊዜም ቢሆን ፣ "በየአንዳንዱ አስራ ሁለት ሐዋርያት፣ አንድ አንድ ይሁዳ አይጠፋም" ከተባለ፣ በአለፉት የአርባ ዓመታት የትግል ታሪኩ፣ ፓርቲው በውጭና በውስጥ ከሃዲያን መከሰት ምክንያት ጥቃት ሊደርስበት ተሞክሯል። በወያኔ የዘር በሽታ በመለከፍም፣

"**ደም ከልጓም ይስባል**" በሚለው ይትበኃል ሰለባ የሆኑ እንዳልጠፉም የሚካድ አይሆንም። የከሃዲዎች ፀረ ድርጅት እንቅስቃሴ ግን የፓርቲውን ኅብረ - ብሄራዊ ይዘትና ስብዕና፣ ባኅርይ ተግባርና ፣ ዓላማ ሊፈታተነው ቀርቶ ፣ ሲያልፍም አልነካው።

የጅብራልታር ቋጥኝ፣ በዓለም የጦርነት ታሪክ ሂደት፣ የማያቋርጥ የውጊያና የጦርነት ዘመቻ መተላለፊያና መራኮቻ በመሆኗ ምክንያት ብዙ ፍዳ ብትቀበልም፣ ያን ሁሉ የጦርነት ማዕባል ተቋቁማ፣ አይበገሬ ቋጥኝነቷ ያው አሁንም ፍንክች ሳይል ይኖራል። በዚህም የተነሳ ብዙ ባለቅኔዎችና የታሪክ ፀሀፊዎች ስለ ጅብራልታር አለት በርካታ መፅሐፍት ደርሰዋል።

ኢሕአፓም በትግል ታሪኩ የተለያዩ ጥቃቶችና በደሎች ተፈራርቀውበታል። ከአምባገነኖች እስከ ሀገር በታኞች፣ ከጠባብ ብሔረተኞች እስከ ፀረ-ኢትዮጵያ ባዕዳን ኃይሎች፣ ተባብረው ሊያጠቁት ሞከረዋል። ሁሉንም እንዳመጣጣቸው ተቋቁሞ ኅልውናውን ጠብቆ፣ ድርጅታዊነፃነቱንና አኩሪ ታሪኩን አስከብሮ ፣ የገባውን ቃል ኪዳን አጠንክሮ ትግሉን ቀጥሏል። ድርጅታዊ ነፃነት ስንል፣ ለከንቱ ውዳሴና ለአልኩ-ባይነት ሳይሆን ፣ በተጨባጭ ማስረጃ እያስረገጥን ነው። የትግላችንም ዓይነተኛው ተልዕኮ ፣ ለማንኛውም የውጭ ኃይል ግፊትና ተፅዕኖ ሳትንበረከክ ነፃነቷን የጠበቀች ኢትዮጵያን ማየት ስለሆነ፣ መጀመሪያ የድርጅትን ነፃነት ማስከበር መሠረታዊ መለያችን ሆኖ ቀጥሏል። ነፃ ሀገር ለመመስረት የሚታገል ድርጅት በበኩሉ የራሱን ድርጅታዊ ነፃነት ሊያረጋግጥ የሚችለው፣ የአባላቱን ነፃነት አክብሮ ሲያስከብር ነው። የራሱን ነፃነት የሚያስከብር ድርጅት፣ የራሱን ነፃነት ብቻ ሳይሆን ያባላቱንም ዴሞክራሲያዊ ነፃነት ጠብቆ ማስከብር እንዳለበት የሚያጠያይቅ አይሆንም። የአርባ ዓመት የትግል ፅናት አብነቱም ይኸው ነው። የራስን ነፃነት ያላከበረ ድርጅት ፣ የሀገርን ነፃነት አስከብራለሁ ለማለት የሚያስችል የሞራል ብቃት ሊኖረው ከቶ አይችልም።

የታሪክን ምፀት መታዘብ ካስፈለገ፣ በፓርቲው ጥቃት ላይ የተባበሩት ሁሉ ፣ ኢሕአፓን እንደ መሥዋዕት ጠቦት ለመጠቀም የሚያደርጉት ሙከራ ነው። ለአለፉት አርባ ዓመታት ለተፈፀሙት ክስተቶች በሙሉ፣ ፓርቲውን እንደተጠያቂ መቁጠር፣ የሥነ- አዕምሮ እፎይታ ይሰጠናል ብለው የሚያስቡ ሁሉ በመተባበር ሲራኮቱ እናያለን ፣ እንሰማለን። ኢሕአፓን ለመሥዋዕት ጠቦት በማቅረብ የሀገራችን ሁለንተናዊ ችግሮች የሚፈቱ ቢሆንማ ኖሮ ፣ ደግሞም ይሆናል ተብሎም ከታመነበት ፣ ፓርቲው ምን ጊዜም ፣ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ እንደ መሥዋዕት ጠቦት ለመቅረብና በግንባር ቀደምነትም ለመሰዋት ምን ጊዜም ቢሆን ወደኋላ እንደማይል አኩሪ ታሪኩ ያረጋግጥለታል። ያም ይሁንና፣ ዛሬ ግን የቅድሚያ የትግል ተልዕኮው፣ ኢትዮጵያን ከዘረኛ አምባገነን ሥርዓት አላቆ ነፃ ማውጣት እንጅ፣ ለግል ታሪክን መመዝገቢያ የሚሆን ፋይል--ዶሴ ማሰናዳት አይደለም። ታጋይ ድርጅት፣ ታሪክ እየሠራ ይሰዋል እንጅ፣ ታሪኬን ማን ይጽፍልኛል ብሎ አይጨነቅም። ምክንያቱም፣ ኢትዮጵያና ሕዝቧ የታሪክ ህውልትና ማኅደር በመሆናቸው የማንኛውንም ታሪክ ዜና-መዋዕል የመመዝገብ ተግባር የእነርሱ ድርሻ ይሆናል ብሎ ስለሚያምን ነው።

በጠቅላላው ፤ እኛ ፤ ኢትዮጵያ፣ ታሪኳም ሆነ ፤ በመልክዐ - ምድሯ ውስጥ የተንጣለለው ሀብቷ፣ የግዛት አንድነቷ፣ የአየር ንብረቷ ፤ በከርሰ ምድሯ የተከማቸው ጥሪቷ በሙሉ ፤ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት በመሆኑ፣ ተጠቃሚነቱ ፤ የሁሉም ዜጋ ነው ስንል፣ እነርሱ ግን ከአድዋ ክልል መውጣት የለበትም ባዮች ናቸው:: በዚህ መሠረታዊ ልዩነት ምክንያት፣ ከመጀመሪያው አንስቶ፣ ከወያኔ ጋር በማይታረቅ ተፃራሪ ጎራ ላይ ተሰልፈናል:: ታዲያ፣ እነርሱ ዛሬ፣“ **ከኢሕአፓ ጋር አጥፊና ጠፊዎች ነን**” ቢሉ የሚያስገርም አልሆነም::

ከባለጊዜ ጋር ተጎናብሰህ እንዲያልፍልህ ማድረግ አለብህ:: ከሚመጣው ሥርዓት ሁሉ ጋር እየተጠጋህ ፤ ራስክን እየጠቀምክ ፤ ቤተሰብህንና ወገንህን ጥቀም:: **ሞኝ አሳላፊ ዘመዱን ይጎዳል እንዳትባል**! ሲሾም ያልበላ ፤ ሲሻር ይቆጨዋል! **ብለው እንዳያፌዙብህ ብልጥ መሆን አለብህ! ወያኔ ከሚበላህ ለወያኔ እያገለገልክ ከማዕዱ ተቋደስ! ትግል ካስፈለገም ፤ እየተገዙ መታገል እንጅ ፤ እያመፁ መታገል ጊዜው ያለፈበት ያረጀ-ያፈጀ ፈሊጥ ነው! ሥልጡን ፖለቲካ አይደለም!** የሚሉትን የእበላ - ባዮች መፈክሮች እንደ ማጠየቂያ በመጠቀም ፤ ራሳቸውን እያዋረዱ፣ ወገኖቻቸውን እያሳፈሩ ፤ ታጋዮችን እየኮነኑ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል እየበደሉ ፤ የታሪክን ሂደት እያወሳሰቡ ፤ ራሳቸውን እየደለሉ ይኖራሉ:: እየኖሩ መሞትን እንጅ፣ እየሞቱ መኖርን፣ በትግል ሕያው መሆንን ሰብዕናቸው ስለማይፈቅድላቸው፣ ታሪክ ሰርቶ ማለፍ ሳይሆን ፤ በታሪክ ጉድፍ ውስጥ ታምቆ መኖርን መርጠዋል:: ይህን አቋም ቢወስዱ ፤ ምርጫው የራሳቸው ነው:: የኢትዮጵያን ሕዝብ የነፃነት ትግል ግን ሊያደፈርሱትም ሆነ አቅጣጫ ሊያስቱት አይፈቀድላቸውም ::

የኢትዮጵያን ሕዝብ የትግል ምርጫ፣ ማለትም፣ ስልት/ዘዴም ሆነ፣ ይዘት፣ አቅጣጫም ሆነ ሂደት፣ መድረሻም ሆነ ውጤት የሚወስነው፣ ራሱ ባለቤቱ የኢትዮጵየ ሕዝብ እንጅ፣ ማንም ባንዳና ባዕዳን አይደሉም:: ይህ መሠረታዊ ሐቅ ከጥንት-ከጧቱ፣ ከቅድመ-ታሪኩ፣ ከባጎሉና ከአባት-ከእናቱ ሲወርድ የመጣና የተመዘገበ ነው:: በመሆኑም ምን ዓይነት የትግል ስልት መኖር እንደሚገባው የኢትዮጵያን ሕዝብ ተፅዕኖ ለማሳደር የሚሞክር ማንም የሞራል ሥልጣንም ይሁን ህጋዊ ውክልና ያለው አይኖርም:: አንድ ሕዝብ ፤ በረዥም ዘመን ታሪኩ፣ ሀገሩን ለባዕድ ወረራ ሳያስደፍር በነፃነት ጠብቆ በማቆየት ለተተኪ ትውልድ ማስተላለፍ የሚችለው፣ ወራሪን ለመከላከል በሚያደርገው የአርነት ተጋድሎና የአርበኝነት አሰላለፍና የውጊያ ስልት ፤ ባዕዳንንም ሆነ ጠላቶችን እያማከረ አይደለም:: ዛሬም ቢሆን ይህን መሠረታዊ ሐቅም ይሁን ነባራዊ ሁኔታ ሊለውጠውና፣ ሊሽረው የሚችል ኃይል አይኖርም:: ዕርግጥ ዛሬ አንድ-አንድ የባዕድ አፈ-ቀላጤዎችና የዘር ፖለቲካን አሜን ብለው የተቀበሉ፣ ተስፋ ቆራጮች፣ “ዓለም በአንድ ልዕለ-ኃያል መዳፍ ቁጥጥር ውስጥ ስለገባችና፣ የዓለም አቀፍ ሁለንተናዊ ሁኔታም፣ ሌላ አቅጣጫ በመያዙ፣ የዚህን ልዕል-ኃያል ፈቃድና ትዕዛዝ አምኖ መቀበልና መገዛት እንደሚያስፈልግ ይሰብካሉ:: ተስፋ ቆርጠው ተስፋ ለማስቀረጥ የሚያስችላቸውንም ዘዴና ስብከት በመጠቀም፣ ታማኝ አገልጋይ ለመሆን የሚያበቃቸውን መስፈርት በማሟላት ላይ ይገኛሉ:: ቀፎው ተነቅንቆ

የወጣን ንብና ለአመፅ ገንፍሎ የወጣን ሕዝብ ሊያቆመው የሚችል አንዳችም ምድራዊ ኃይል ስለማይኖር ፣ ይዘግይም ይፍጠን ፣ የኢትዮጵያ ትንሣዔ መምጣቱ አይቀሬ ነው:: ወያኔዎች፣ "ዉሾቹም ይጮሃሉ ፣ ግመሉም ይጓዛል! " ብለው እንደቀለዱ አይኖሩም:: **ልብ ያለው ልብ ይበል**!

የሀገራችን ትንሣዔ መምጣቱ አይቀርም ሲባል ግን ፣ የተባበረና በውጤት ላይ ያተኮረ ሀገር-አቀፍ ትግል ማካሄድ ወሳኝና አንገብጋቢ መሆኑ መታወቅ አለበት:: የኢትዮጵያን ትንሣዔ የሚመኝ ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣ ከማንኛውም ጉዳይ በበለጠ ቅድሚያ መስጠት ያለበት ወያኔን ተቃውመው የቆሙ ሀቀኛ የአንድነት ኃይሎች በሞላ ፣ በተግባር በትግሉ መስክ ኅብረት ፈጥረው መታገል አለባቸው የሚለው ሕዝባዊ ጥሪ ወቅታዊ፣ እንዲሁም አንገብጋቢና ወሳኝ መሆኑን ነው:: "ኅብረት ኅብረት" ተብሎ ስለተዘመረ ብቻ ጠንካራና፣ ዘላቂ ኅብረት ሊመጣ እንዳልቻለ በአለፉት ሃያ ዓመታት የታየ ነው:: ወያኔ ፣ ምንሊክ ቤተ መንግሥት ውስጥ በመመሽግ፣ ኢትየጵያን ማጥፋት ሕዝቧንም መከፋፈል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ፣ ተቃዋሚ ኃይሎች ኅብረት ለመፍጠር ስድስት ልዩ ልዩ ጉባዔዎችን አካሂዋል:: በነዚህ የስብሰባ ጥረቶች ሂደት፣ ቁጥራቸው በየጊዜው ከአምስት እስከ አስራ ስድት የሚደርሱ ድርጅቶች እየተሰባሰቡ ፣ የጋራ ሰነድ እየነደፉ፣ በጋራው ሰነድ መሠረት፣ አብረው ሊታገሉ እየተስማሙ፣ ምለው ተገዘተው ከተፈራረሙ በኋላ ፣ የፊርማቸው ቀለም ከመድረቁ በፊት እንደ ልጆች ጨዋታ፣ "ዳቦው ተቆረሰ፣ ጨዋታው ፈረሰ" እንዲሆን ተደረገ:: በዚህ ምክንያት ብዙ ድካምን የጠየቀው የኅብረቱ ዓላማ ግብን ሳይመታ መና ሆኖ ቀረ:: ይህ ክስተት ሁለት ጠባሳዎችን ጥሎ ሄዷል:: አንደኛው፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ የለመለመ ተስፋ እንዲጠወልግ ምክንያት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ወያኔዎችን የልብ ልብ ሰጥቷቸው፣ ኢትዮጵያን እንደ "ገል ቀጥቅጠን እንደ ሰም አቅልጠን መግዛት ችለናል" ብለው የድንቁርና ትዕቢት እንዲሰማቸው አድርጓል:: ይህ ብሔራዊ ጥቃት፣ ሀገራዊ ውርደትና ታሪካዊ ዕልመት የማይሰማው ኢትዮጵያዊ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም:: ኢሕአፓ "**ብልኅ ከስኅተቱ ይማራል**" የሚለውን ይትብኃል ከልብ ስለሚያምንበት ወያኔን ተፃርረው የቀሙ የአንድነት ኃይሎች ፣ እንደ ገና በመሰባሰብ ፣ የኅብረቱን ጉዳይ የትግላቸው አካል እንዲያደርጉት በየጊዜው ወቅታዊ ጥሪዎችን አቅርቧል::

ይህ ለኅብረት ትግል የምናደርገው ጥሪ ሁለት ዓበይት ጉዳዮችን መሠረት ያደረገ ነው::

<u>አንደኛው</u> :- የሀገራችን ውስብስብና ሥር የሰደዱ ችግሮች መፍትሄ የሁሉንም ድርጅቶች የተባበረ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው:: አንድ ወይም ፣ ጥቂት ድርጅቶች ብቻቸውን ተጠራርተው ብዙውን የሀገሪቱ ኃይል በማግለል የፖለቲካ ጥሎ ማለፍ ጨዋታ ብቻ እየተጫወቱ ቢቀጥሉ፣ የሀገራችንን የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች መፍታት ቀርቶ ሊቀረፍቷቸው አይችሉም:: ይህንን የፖለቲካ ቁማር ጨዋታ ወያኔም ለላለፉት ሀያ ዓመታት ሞክሮት አልተሳካለትም:: የሀገሪቱን ችግር መፍታት የሚችሉት ኢትዮጵያውን ሁሉ ሳይከፋፈሉና ሳይነጣጠሉ በአንድ ላይ ሲያስቡና ሲወያዩ ብቻ መሆኑን ለማወቅ ጠቢብ መሆንን የሚጠይቅ አይደለም:: የችግርን ዕምብርት ፈልፍሎ በማውጣትና በግልፅ መወያየት፣ ለመፍትሄው ፍለጋ

*የመጀመሪያ እርምጃ መሆኑን ማጤን ጠቃሚነቱ ፣ ወያኔን ገፍትሮ ለመጣል ብቻ ሳይሆን በድህረ-ወያኔ ለምትመጣው ሀገራችን ላለው ሁለንተናዊ ሁኔታም፣ ኃላፊነቱን በጋራ ለመሸከምም ጭምር ይረዳል ብለን እናስባለን። ኢትዮጵያዊ መርህ-ግብርን አንግቦ መታገል፣ ወሳኝ ሊሆን የሚችለው ሁሉንም ያካተተ ፣ ያቀፈና ያስተባበረ ብሔራዊ የነፃነት ግንባር ነጥሮ ሲወጣ መሆኑን አምኖ መቀበል ማለት፣ የወያኔን አከርካሪ አጥንት ቆምጦ መጣል ማለት ነው። በመሆኑም፣ ኢትዮጵያዊ መርህን ያነገበው ሁሉ ተሰባስቦ በኅብረት ከመታገል የተለየ ምርጫ ሊኖረው አይችልም ።*

*<u>ሁለተኛው</u>፦ ያለፉት አርባ የትግል ዓመታት ያስተማሩን ዓበይት ትምህርቶች ቢኖሩ፣ አምባገነኖችን አስወግዶ ፣ በምትካቸው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት፣ ቀላል አለመሆኑን ነው። ከዚህ የበለፀገ የትግል ተመክሮ በመነሳት፣ አያሌ መሠረታዊ ሁኔታዎችን ለማጤን ዕድል ስጥቶናል ብለን በትህትና ለማመን እንገደዳለን። ትግሉ ውስብስብ፣ ጠመዝማዛና ከአንድ ሰው ዕድሜ በላይ ሊወስድም እንደሚችል አምኖ መቀበል ብቻ ሳይሆን፣ ከፍተኛ የሕይወት መሥዋዕትንም የሚጠይቅ መሆኑንም ለመረዳት ችለናል። በሂደቱም፣ በርካታ የኃይል አሰላለፎች፣ የአቋም መንሸራተቶች ፣ የዕምነትና ክኅደት ክስተቶች ፣ በድል መቀዳጀትና በሽንፈት መጠቃት፣ የሀገር ውስጥ ፣ የአካባቢና የዓለም አቀፍ ሆኔታ መለዋወጦች ፣ በጠላትና በወገን ጎራዎች መካከል በሚፈጠሩ ዱብዳዎች መንስዔ የዕምነት መዛባቶች ፣ ትግሉ እየመረረ በሚመጣበት ወቅት ከማፈግፈግ ጀምሮ እስናካቴው ትግሉን ትቶ እስከመሄድ ያሉትን ሁሉ ተመክሮዎች ለማየት ችለናል። ይህንን ሁሉ በግምት ውስጥ ማስገባትና ኅብረት ፈጥሮ ተባብሮ መታገል የአንድነት ኃይሉን የትግል ሂደት ያፋጥነዋል ብለን እንገምታለን። የኢትዮጵያን ችግር ውስብስብነትና የትግሉንም ሂደት ጠመዝማዛነት፣ ከመጀመሪያ አስቦ የተባበረ የአንድነት ኃይሎች ኅብረት፣ ይፍጠንም ይርዘም፣ በመጨረሻ ድልን እንደሚቀዳጅ ብዥታ ሊኖር አይችልም።*

*በነዚህ ሁለት አበይት ምክንያቶች መሠረት ነው የአንድነት ኃይሉ በኅብረት መታገል ወሳኝ ነው የምንለው። የአንድነት ኃይሎች ኅብረት ስንል፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ የማይደራደሩትንና በወያኔ ላይ የማያወላውል አቋም ያላቸውን ኃይሎች ማለታችን ነው። በቀቢፀ-ተሰፋ ብዥታ እራስን እየደለሉ፣ ከወያኔ ጋር አብሮ በመሥራት የኢትዮጵያን መፃዒ ዕድል መለወጥ ይቻላል ሲሉ የነበሩት ሁሉ ፣ የሀገሪቱን መፃዒ ዕድል መለወጥ ቀርቶ ፣ የራሳቸውንም ኅልውና ማስከበርና ማዳን እንኳን አልተቻላቸውም። ከዚህ መራራ ተመክሮ በመነሳት አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ምሁራንና ሀገር ወዳድ ዜጎች ፣ ዛሬ ፣ ወያኔን አስመልክቶ፣ ከማያወላውል አቋም ላይ የደረሱና በሀገራችውም ብሔራዊ ጥቅም ላይ ያልተዛባ ውሳኔ በመውሰድ ላይ ይገኛሉ። ይህም ሁኔታ የኢትዮጵያን ሕዝብ ተስፋ እያለመለመው በመሄድ ላይ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ፣ ቀደም ሲል፣ እስቲ ለወያኔ ዕድል እንስጠው፣ ካስፈለገም፣ “**እየተገዙ መታገል**” የሚል ፈሊጥ አንገበው የነበሩ ጥቂት ግለሰቦች፣ የወያኔዎችን ዕውነተኛ ማንነት በሚገባ በመረዳታቸው ዛሬ፣ “ተገዝቶ መታገል!” ከሚለው አቋማቸው፣ ተላቅቀው፣ “**የወያኔ ሥርዓት***

**ካልጠፉ ኢትዮጵያ አትድንም"** ወደሚል አቋም በመሸጋገር ላይ ናቸው። ይህንን መፈክር ወደ ተግባር የሚለውጡት ከሆነ፣ ወደፊት የሚታይ ቢሆንም ቅሉ ፣ ኢትዮጵያን ከዘረኞች መንጋጋ ለማላቀቅ ግን የመልካም አቅጣጫ ሂደት እንደሚሆን ይገመታል።

ኢሕአፓ ትግል የጀመረበትን አርባኛ ዓመት ስናከብር፣ በአንድ በኩል፣ ደስታና ክብር ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሀዘንና ቁጭት እየተሰማን ነው። ደስታና ክብር ስንል፣ ለሕዝባችንና ለሀገራችን የገባነውን ብሔራዊ ቃል-ኪዳን በማክበር የደረሰብንን የትግል ውጣ-ውረድና ከፍተኛ መሥዋዕት ሁሉ ተቋቁመን እዚህ በመድረሳችንና አሁንም እንደ ትላንቱ የትግል ቱማታችን እየጋለ በመሄዱ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከደረሰባት ውርደት ነፃ እስክትወጣ ድረስ፣ ትግላችንን ለመቀጠል ቃል ኪዳናችንን የምናድስ በመሆናችን ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሀዘንና ቁጭት ከልብ ይሰማናል የምንለው፣ ዕልፍ-አዕላፍ ሰማዕታት ጓዶቻችንን በማስታወስና ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ በጠላቶቿ እየደረሰባት ያለውን ሀገራዊ ጥቃትና ብሔራዊ ውርድት በማየት ነው። ያም ይሁንና፣ የገባነውን የትግል ቃል-ኪዳን በመቀጠል፣ ሀዘናችንና ቁጣችን ወደ ድል እስከተለወጠ ድረስ ፣ ትግሉ የሚጠይቀውን ማንኛውንም መሥዋዕት በመክፍል ትግላችንን ለመቀጠል የገባነውን ቃል-ኪዳን ለማክበር ግንባራችንን አናጥፍም። ከኢትዮጵያ ሀገራችንና ሕዝባችንም ጎን ተሰልፈን:-

> "አይነኩም አይነካኩም፣ የኢትዮጵያን ጎፈሬ፣ የኢትዮጵያን ቆንዳላ፣
> የሕዝቧንም ቁንጮ ፣ የልጆቿን ጋሜ፣ የወጣቷን ሳዱላ፣
> ጣጣዋ ብዙ ነው የኋላ የኋላ ፣ እሾ኿ም መርዝ ነው እንደኮሸሽላ !"

በማለት ትግላችንን እንቀጥላለን።

ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኑር !
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!
እናቸንፋለን!